### የቂጣ በዓል

3 ሙሴም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤ “ይህ ቀን
በባርነት ስትገዙ የኖራችሁበትን የግብጽን
ምድር ለቃችሁ የወጣችሁበት ስለሆነ ይህን
ቀን አስታውሱ፤ እግዚአብሔር በታላቅ ኀይሉ
በመታደግ ያወጣችሁ በዚህ ቀን ነው፤ ስለዚህ
በዚህ ቀን እርሾ የነካው እንጀራ አትብሉ።
4 በዚህ ቀን፣ የዓመቱ መጀመሪያ በሆነው በአ
ቢብ ወር ግብጽን ለቃችሁ ወጥታችኋል። 5 የከ
ነዓናውያንን፣ የሒታውያንን፣ የአሞራውያ
ንን፣ የሒዋውያንንና የኢያቡሳውያንን ምድር
እንደሚያወርሳችሁ እግዚአብሔር ለቀድሞ አባ
ቶቻችሁ በመሓላ ቃል ኪዳን ገብቶአል፤ ማርና
ወተት ወደምታፈሰው ወደዚያች ለም ምድር
በሚያገባችሁ ጊዜ በዓመቱ መጀመሪያ ወር ላይ
ይህን በዓል ታከብሩታላችሁ። 6 ሰባት ቀን
ሙሉ እርሾ የሌለበት ቂጣ ትበላላችሁ፤ በሰባተ
ኛውም ቀን ለእግዚአብሔር ክብር በዓል ታደር
ጋላችሁ። 7 እስከ ሰባት ቀን ድረስ እርሾ የነ
ካው እንጀራ አትበሉም፤ እርሾም ሆነ የቦካ
እንጀራ ከቶ በምድራችሁ አይገኝ። 8 በዓሉም
በሚከበርበት ጊዜ ይህን ሁሉ የምታደርጉት
ከግብጽ በወጣችሁበት ጊዜ እግዚአብሔር ያደረ
ገላችሁን መልካም ነገር ሁሉ ለማስታወስ መሆ
ኑን ለልጆቻችሁ ተርኩላቸው። 9 ይህም በዓል
በእጃችሁ እንደታሰረና በግንባራችሁ ላይ እንደ
ሚገኝ ምልክት ማስታወሻ ይሆንላችኋል፤ እግ
ዚአብሔር በታላቅ ኀይሉ ከግብጽ ስላወጣች
ሁም የእግዚአብሔር ሕግ ዘወትር ከአንደበታ
ችሁ ሳይለይ በቃላችሁ እንድትደግሙትና እን
ድታጠኑት ያስታውሳችኋል። 10 ስለዚህ ይህን
በዓል በየዓመቱ በተመደበለት ቀን አክብሩት።

### የበኵር ልጅ

11 “እግዚአብሔር ለእናንተና ለቀድሞ አባቶ
ቻችሁ ለመስጠት ቃል ወደገባላችሁ ወደ ከነዓ
ናውያን ምድር ያመጣችኋል፤ ይህችንም
ምድር በሚያወርሳችሁ ጊዜ፣ 12 በኵር የሆነ
ውን ወንድ ልጅ ሁሉ ለእግዚአብሔር ትሰጣላ
ችሁ፤ እንዲሁም የእንስሶቻችሁ በኵር ሁሉ
ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናል። 13 ከአህያ የተ
ወለደውን በኵር ግን የበግ ጠቦት በመተካት ከእ
ግዚአብሔር እጅ ትዋጁታላችሁ፤ አህያውን
ለመዋጀት ካልፈለጋችሁ ግን አንገቱን ስበሩት፤
በኵር የሆነውንም ወንድ ልጅ ሁሉ ከእርሱ
እጅ መዋጀት ይገባችኋል። 14 በሚመጡት ዘመ
ናት ወንድ ልጅህ የዚህን ሥርዓት ትርጉም
ቢጠይቅህ እንዲህ በማለት ታስረዳዋለህ፤ ‘በባር
ነት ከተገዛንበት ከግብጽ ምድር እግዚአብሔር
በታላቅ ኀይል አወጣን፤ 15 የግብጽ ንጉሥ
ልቡን አደንድኖ እልኸኛ በመሆን አልለቃች
ሁም ባለ ጊዜ እግዚአብሔር በግብጽ ምድር
የሰውንም ሆነ የእንስሳትን በኵር ሁሉ ገደለ፤
በኵር ሆኖ የተወለደውን ወንድ እንስሳ መሥዋ
ዕት አድርገን የምናቀርበው በዚህ ምክንያት
ነው፤ በኵር ሆነው የተወለዱትን ወንዶች ልጆ
ቻችንን ግን እንዋጃቸዋለን። 16 ይህም ሥርዓት
በእጃችን እንደታሰረና በግንባራችን ላይ እንደሚ
ገኝ ምልክት ማስታወሻ ይሆናል፤ እግዚአብ
ሔር በታላቅ ኀይሉ ከግብጽ ምድር እንዳወጣ
ንም ያስታውሰናል።’ ”

### የደመና ዐምድና የእሳት ዐምድ

17 የግብጽ ንጉሥ ሕዝቡን በለቀቀ ጊዜ፣
እግዚአብሔር ቅርብ በሆነው በፍልስጤም የባ
ሕር ጠረፍ በኩል ባለው መንገድ አልመራቸ
ውም፤ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ሕዝቡ
ከፊት ለፊታቸው ጦርነት እንደሚጠብቃቸው
ባዩ ጊዜ አሳባቸውን ለውጠው ወደ ግብጽ እን
ዳይመለሱ ነው። 18 ስለዚህ ይህን በማድረግ
ፈንታ ወደ ቀይ ባሕር በሚያመራው በረሓ፣
ዙሪያ ጥምጥም በሆነ መንገድ መራቸው፤ እስ
ራኤላውያንም ለጦርነት እንደተዘጋጁ ሆነው
ከግብጽ ወጡ።
19 ዮሴፍ እስከሬኑን እንዲወስዱ እስራኤላው
ያንን በመሐላ ቃል ኪዳን ባስገባቸው መሠረት
ሙሴ የዮሴፍን አስከሬን ይዞ ሄደ፤ ምክንያቱም
ዮሴፍ “እግዚአብሔር ታድጎአችሁ በምትወጡ
በት ጊዜ ዐፅሜን ከዚህች ምድር ይዛችሁ እንድ
ትወጡ” በማለት ተናግሮ ነበር።
20 እስራኤላውያን ከሱኮት ተነሥተው በበረ
ሓው ዳርቻ በምትገኘው በኤታም ሰፈሩ፤
21 ቀንና ሌሊት መጓዝ ይችሉ ዘንድ፣ እግዚአብ
ሔር ቀን በደመና ዐምድ፣ ሌሊት ደግሞ ብር
ሃን በሚሰጥ በእሳት ዐምድ ይመራቸው ነበር፤
22 በዚህ ዐይነት የደመናው ዐምድ በቀን፣ የእ
ሳቱ ዐምድ በሌሊት ዘወትር እፊት እፊታቸው
ይገኝ ነበር።

## ምዕራፍ 14

### ቀይ ባሕርን መሻገር

1 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2 “እስራኤላውያን ተመልሰው፣ በሚግ
ዶልና በቀይ ባሕር መካከል ባለው ፊሃሒሮት
ፊት ለፊት በበዓልጻፎን አጠገብ እንዲሰፍሩ ንገ
ራቸው። 3 እነሆ ንጉሡ እስራኤላውያን በበረሓ
ተዘግተው በአገሪቱ ዙሪያ የሚንከራተቱ ይመስ
ለዋል። 4 እኔም ልቡን በማደንደን እልኸኛ ስለ
ማደርገው ያሳድዳችኋል፤ ስለዚህም በንጉሡና

---

13፥12 ፡- ዘጸ. 34፥19-20፤ ሉቃ. 2፥23። 13፥19 ፡- ዘፍ. 50፥25፤ ኢያሱ 24፥32።

እስከ መሠዊያው እኩሌታ እንዲደርስ ከመሠዊ
ያው ክፈፍ በታች አድርገው፤ 6ለመሠዊያው
መሸከሚያ የሚሆኑ መሎጊያዎችንም ሠርተህ
በነሐስ ለብጣቸው። 7መሠዊያውን መሸከም
በሚያስፈልግበትም ጊዜ መሎጊያዎቹን ከመሠ
ዊያው በእያንዳንዱ ጐን ባሉት ቀለበቶች
ውስጥ አግባ። 8በተራራው ላይ ባሳየሁህ ዕቅድ
መሠረት መሠዊያውን ከሳንቃዎች ሥራ፤ ውስ
ጡም ባዶ ይሁን።

### የድንኳኑ አደባባይ ክልል
(ዘጸ. 38፥9-20)

9"ለድንኳኑ አደባባይ ክልል መጋረጃዎች
ከቀጭን ሐር ሥራ፤ የመጋረጃዎቹም ርዝመት
ከደቡብ በኩል አርባ አራት ሜትር ይሁን፤
10ለእርሱም መደገፊያ ሃያ የነሐስ እግሮች ያሉ
ቸው ሃያ ምሰሶዎች ሥራ፤ በእነርሱም ላይ
ከብር የተሠሩ ዘንጎችና ኩላቦች ይኑሩ፤
11በስተ ሰሜን በኩል ላለውም አደባባይ ልክ
በዚሁ ዐይነት ይሠራ። 12በምዕራብ በኩል አደ
ባባይ ዐሥር እግሮች ካሉአቸው ዐሥር ምሰሶ
ዎች ጋር ርዝመታቸው ሃያ ሁለት ሜትር የሚ
ሆን መጋረጃዎች ይኑሩት። 13የመግቢያው በር
ባለበት በምሥራቅ በኩል የአደባባዩ ስፋት ሃያ
ሁለት ሜትር ይሁን። 14-15በመግቢያው በር
ግራና ቀኝ ርዝመታቸው ስድስት ሜትር ከስ
ልሳ ሳንቲ ሜትር የሆነ መጋረጃዎች ይኑሩ፤
ሦስት እግሮች ያሉአቸው ሦስት ምሰሶዎችም
ይደግፉት። 16ለራሱ ለመግቢያው በር ርዝመታ
ቸው ዘጠኝ ሜትር የሆነ ከሰማያዊ፥ ከሐምራ
ዊና ከቀይ ግምጃ ከተፈተለ ከጥሩ በፍታ የተሠ
ሩና በጥልፍ ያጌጡ መጋረጃዎች ይኑሩት፤
የሚደግፉትም አራት እግሮች ባሉአቸው አራት
ምሰሶዎች ይኑሩት። 17በአደባባዩ ዙሪያ ያሉት
ምሰሶዎች ሁሉ በብር ዘንጎች ይያያዙ፤ ኩላቦቻ
ቸው ከብር፥ እግሮቻቸውም ከነሐስ የተሠሩ
ይሁኑ። 18የድንኳኑ አደባባይ ርዝመቱ አርባ
አራት ሜትር የጐኑ ስፋት ሃያ ሁለት ሜትር፥
ከፍታውም ሁለት ሜትር ከሃያ ሳንቲ ሜትር
ይሁን፤ መጋረጃዎቹ ከጥሩ በፍታ የተሠሩ
ሆነው የነሐስ እግሮች ይኑሩአቸው።
19በድንኳኑ ውስጥ የሚገኙት ለማናቸውም
ጥቅም የሚውሉ የመገልገያ ዕቃዎች ሁሉ፥
የድንኳኑና የአደባባዩ ካስማዎች ሁሉ ከነሐስ
የተሠሩ ይሁኑ።

### ስለ መብራት የሚደረግ ጥንቃቄ
(ዘሌ. 24፥1-4)

20"መብራቱ በየምሽቱ ሲበራ እንዲኖር
ለመብራት የሚሆነውን ምርጥ የወይራ ዘይት
ያመጡልህ ዘንድ የእስራኤልን ሕዝብ እዘዝ፤
21አሮንና ልጆቹ እኔ በምመለከበት ድንኳን
ውስጥ መብራቱን ያሰናዱት፤ በፊቱ ከምሽት
እስከ ንጋት ይበራ ዘንድ ከቃል ኪዳኑ ታቦት
ፊት ለፊት ካለው መጋረጃ ውጭ ያኑሩት፤
ይህም የሕግ መመሪያ በእስራኤል ሕዝብና ወደ
ፊትም በሚነሣው ትውልድ ዘንድ ለዘላለም
ተጠብቆ ይኑር።

## ምዕራፍ 28

### ልብሰ ተክህኖ
(ዘጸ. 39፥1-7)

1"ወንድምህን አሮንንና ልጆቹን ናዳብን፥
አቢሁን፥ አልዓዛርንና ኢታማርን ወደ አንተ
አቅርብ፤ ካህናት ሆነው ያገለግሉኝም ዘንድ
ከእስራኤል ሕዝብ መካከል ለያቸው። 2ለክብ
ርና ለውበት ይሆነው ዘንድ ለወንድምህ ለአሮን
የክህነት ልብስ ሥራለት። 3እኔ ልዩ ችሎታ
እንዲኖራቸው ያደረግሁአቸውን የእጅ ጥበብ
ዐዋቂዎችን ጠርተህ ለአሮን ልብስ እንዲሠሩለት
ንገራቸው፤ በዚህ ዐይነት አሮን ካህን በመሆን
ያገለግለኝ ዘንድ ለእኔ የተለየ ይሆናል። 4በዐይ
ነት የሚሠሩአቸውም ልብሶች እነዚህ ናቸው፤
የደረት ኪስ፥ ኤፉድ፥ ቀሚስ፥ በጥልፍ ያጌጠ
ሸሚዝ፥ ጥምጥምና መታጠቂያ፤ ወንድምህ
አሮንና ልጆቹ ካህናት ሆነው ያገለግሉኝ ዘንድ
እነዚህን ልብሶች ይሥሩላቸው። 5ጥበበኞቹም
ልብሶቹን ከሰማያዊ፥ ከሐምራዊ፥ ከቀይ
ግምጃ፥ ከወርቅ ምዝምዝና ከጥሩ በፍታ በጥ
ልፍ አስጊጠው ይሥሩ።

6"ኤፉድንም ከሰማያዊ፥ ከሐምራዊ ከቀይ
ግምጃ፥ ከወርቅ ምዝምዝና ከጥሩ በፍታ በጥ
ልፍ አስጊጠው ይሥሩ። 7ሁለቱ ወገን አንድ
እንዲሆን በሁለቱ ትከሻ ላይ የሚጋጠም የጥብ
ጣብ ዐይነት ማንገቻ ይኑር። 8ኤፉዱ ከተሠራባ
ቸው ተመሳሳይ ነገሮች በብልኀት የተጠለፈ
መታጠቂያ አንድ ላይ እንደተሠራ ሆኖ ከኤ
ፉዱ ጋር ይጣበቅ። 9ሁለትም የመረግድ ድን
ጋይ ወስደህ የዐሥራ ሁለቱን የያዕቆብ ልጆች
ስም ቅረጽባቸው፤ 10ይኸውም የልደታቸውን
ቅደም ተከተል ሳታፋልስ ስድስቱን በአንድ
ድንጋይ ላይ፥ ስድስቱንም በሌላ ድንጋይ ላይ
ጻፍ። 11በሁለቱ ድንጋዮች ላይ የዐሥራ ሁለ
ቱን የያዕቆብ ልጆች ስሞች ለመቅረጽም
ችሎታ ያለው ብልኅ ሰው አግኝ፤ ድንጋዮቹ
ንም ከወርቅ በተሠራ ፈርጥ ላይ አኑራቸው።
12ለዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች መታሰ
ቢያ ይሆኑ ዘንድ ሁለቱን ዕንቍዎች በትከሻ
ላይ በሚያልፉት የኤፉድ ማንገቻዎች ላይ ታደ
ርጋቸዋለህ። በዚህ ዐይነት እኔ እግዚአብሔር
ዘወትር ሕዝቤን አስታውስ ዘንድ አሮን የእነር
ሱን ስሞች በትከሻው ይሸከማል። 13ሁለት የወ
ርቅ ፈርጦች ሥራ፤ 14እንደ ገመድ ተጉንጉ
ነው ከንጹሕ ወርቅ የተሠሩ ሁለት ድሪዎችንም

አበጅተህ ከሁለቱ ፈርጦች ጋር እንዲያያዙ አድ
ርግ ።

## የደረት ኪስ
(ዘጸ. 39፥8-21)

15 “የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚጠየቅበትን
የደረት ኪስ ለሊቀ ካህናቱ ሥራ፤ አሠራሩ
እንደ ኤፉድ ሆኖ በተመሳሳይ ጥልፍ ያጌጠ
ይሁን ። 16 ርዝመቱ ሃያ ሁለት ሳንቲ ሜትር
የጐኑም ስፋት ሃያ ሁለት ሳንቲ ሜትር ሆኖ
ታጥፎ የተደረበ ትክክል አራት ማእዘን
ይሁን ። 17 አራት ረድፍ የሆነ የዕንቊ ፈርጥ
አድርግበት፤ በመጀመሪያው ረድፍ ሰርድ
ዮን፥ ቶጳዝዮንና፥ የሚያብረቀርቅ ዕንቊ፥
18 በሁለተኛው ረድፍ በሉር፥ ሰንፔርና ሀል
ማዝ፤ 19 በሦስተኛው ረድፍ ያክንት፥ ኬልቄ
ዶንና አሜቴስጢኖስ፥ 20 በአራተኛው ረድፍ
ቢረሌ፥ መረግድና ኢያስጲድ ዘወርቅ ፈርጥ
ላይ ይቀመጣሉ ። 21 ለእስራኤል ነገዶች መታ
ሰቢያ ይሆኑ ዘንድ ከእነዚህ ዐሥራ ሁለት
የዕንቊ ድንጋዮች በእያንዳንዱ ላይ ከያዕቆብ
ልጆች የአንዱ ስም ይቀረጽበታል ። 22 ለደ
ረት ኪሱም እንደ ገመድ የተጐነጐነ ድሪ
ከንጹሕ ወርቅ ሥራ ። 23 ሁለት የወርቅ ቀለ
በቶች ሠርተህ በደረት ኪሱ ከላይኛው ማእ
ዘን በኩል እንዲጋጠሙ አድርግ ። 24 ሁለቱን
የወርቅ ድሪዎች ከሁለቱ ቀለበቶች ጋር አያ
ይዛቸው ። 25 በሌላ በኩል ያሉትንም የሁለ
ቱን ድሪዎች ጫፎች ከሁለቱ ፈርጦች ጋር
አገናኛቸው፤ በዚህም ዐይነት ከፊት ለፊት
በኩል በትከሻ ላይ ከሚወርዱት ከኤፉዱ
ማንገቻዎች ጋር ታያይዛቸዋለህ፤ 26 እንደገ
ናም ሁለት የወርቅ ቀለበቶች ሠርተህ በው
ስጥ በኩል ከኤፉዱ ቀጥሎ ባለው የደረት
ኪስ ከታችኛዎቹ ማእዘኖች ጋር እንዲገጣ
ጠሙ አድርግ ። 27 ከነዚህም ሌላ ሁለት
ተጨማሪ የወርቅ ቀለበቶች ሠርተህ ከፊት
ለፊት በኩል በትከሻ ላይ ከሚወርዱት ከኤ
ፉዱ ማንገቻዎች ጋር ከታች በኩል ታያይዛ
ቸዋለህ፤ መያያዣ ያለበትም በስፌቱ መጋጠ
ሚያ አጠገብና በብልኀት ከተጠለፈው መታ
ጠቂያ በላይ በኩል ነው ። 28 በደረት ኪሱ
ላይ ያሉትን ቀለበቶች በኤፉዱ ላይ ካሉት
ቀለበቶች ጋር በሰማያዊ ድሪ አሰራቸው፤
በዚህ ዐይነት የደረት ኪሱ ከመታጠቂያው
በላይ ስለሚሆን ልል አይሆንም ።
29 “አሮን ወደ ተቀደሰው ስፍራ ሲገባ የእ
ስራኤል ነገዶች ስሞች የተቀረጹበትን ይህን
የደረት ኪስ ይለብሳል፤ በዚህ ዐይነት እኔ
እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሕዝቤን አስታውሳ
ለሁ ። 30 ዑሪምና ቱሚም የተባሉትን ነገሮች
በደረት ኪሱ ውስጥ ታስገባቸዋለህ፤ አሮንም
ወደ ቅዱሱ ድንኳን ሲገባ በደረት ኪሱ ተሸ
ክሞአቸው ይግባ፤ የእኔን ፈቃድ ለእስራኤል
ሕዝብ ማስታወቅ ይችል ዘንድ በፊቴ ለማገል
ገል በሚገባበት ጊዜ ሁሉ በደረት ኪሱ ያድ
ርጋቸው ።

## ሌሎች የክህነት አልባሳት
(ዘጸ. 39፥22-31)

31 “በኤፉዱ ላይ የሚደረበው ቀሚስ ሙሉ
በሙሉ ከሰማያዊ በፍታ የተሠራ ይሁን፤
32 የራስ ማጥለቂያ አንገትጌም ይኑረው፤ ይህም
አንገትጌ እንዳይተረተር ወደ ውስጥ ታጥፎ
በእጅ ሥራ የተቀመቀመ ይሁን ። 33-34 በታች
ኛው ዘርፍ ዙሪያ ከሰማያዊ፥ ከሐምራዊና
ከቀይ ግምጃ የተሠሩ የሮማን ፍሬ ቅርጽ አድር
ግበት፤ በፍሬዎቹ መካከል ጣልቃ የሚገቡ
ከወርቅ የተሠሩ ትናንሽ ቃጭሎች አድርግ
በት ። 35 አሮን በክህነት በሚያገለግልበት ጊዜ
ይህን ቀሚስ ይልበስ፤ በተቀደሰው ስፍራ በፊቴ
በተገኘ ጊዜ ወይም ከዚያ በሚወጣበት ጊዜ
የቃጪሎቹ ድምፅ ስለሚሰማ ከመሞት ይድ
ናል ።
36 “ከንጹሕ ወርቅ አንድ ጌጥ ሥራና በላዩ
ላይ ‘ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለየ’
የሚል ቃል ቅረጽበት ። 37 በመጠምጠሚያውም
ላይ በሰማያዊ ድሪ እንዲንጠለጠል አድርግ፤
38 አሮንም በግንባሩ ላይ ያድርገው፤ በዚህ ዐይ
ነት ባቀራረብ እንኳ ስሕተት ቢፈጽሙ እስራኤ
ላውያን የሚያቀርቡልኝን መባ ሁሉ እኔ እግዚ
አብሔር እቀበላቸዋለሁ ።
39 “የአሮንን ሸሚዝና መጠምጠሚያ ከጥሩ
በፍታ ሥራው፤ መታጠቂያውም ከጥሩ በፍታ
ተሠርቶ በጥልፍ ጥበብ ያጌጠ ይሁን ።
40 “ለአሮንም ልጆች ክብርና ውበት ይሆንላ
ቸው ዘንድ ሸሚዞችን፥ መታጠቂያዎችንና ቆብ
ችን ሥራላቸው ። 41 እንግዲህ እነዚህን ልብሶች
ለወንድምህ ለአሮንና ለልጆቹ አልብሳቸው፤
በክህነት ያገለግሉኝም ዘንድ የወይራ ዘይት
በመቀባት የክህነትን ማዕርግ ትሰጣቸዋለህ፤
ትቀድሳቸዋለህም፤ 42 የውስጥ ሰውነታቸው እን
ዳይጋለጥ ከጥሩ በፍታ፥ ከወገባቸው እስከ ጭና
ቸው የሚደርስ ቁምጣ ሱሪ ትሠራላቸዋለህ፤
43 አሮንና ልጆቹ ዘወትር ወደ ቅዱሱ ድንኳን
ሲገቡ ወይም በተቀደሰው ስፍራ በክህነት ለማገ
ልገል ወደ መሠዊያው ሲቀርቡ ይለብሱታል፥
በዚህ ሀይነት የውስጥ ሰውነታቸው ስለማይጋ
ለጥ ከሞት ይድናሉ፤ ይህ እንግዲህ ለአሮንና
ለዝርያዎቹ ሁሉ ጸንቶ የሚኖር የሥርዓት
መመሪያ ነው ።

28፥30 ፦ ዘኊ. 27፥21 ፣ ዘዳ. 33፥8 ፤ ዕዝ. 2፥63 ፣ ነህ. 7፥65 ።

